# G-SC[H19-67 C]

## የመጀመሪያ መንፈቀ ዓመት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ሞዴል ፈተና

የጥያቄው ብዛት፡- 40 የተፈቀደው ሰዓት፡- 1:00

***መመሪያ***

ይህ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የጉድኝት ፈተና ነው።ይህ ፈተና ስልሳ ጥያቆዎች አሉት። ፈተናውም ሶስት ትዕዛዞች እና ሰባት የገጽ ብዛት አለው። ለእያንዳንዱ ጥያቄም አራት አማራጮች ይዘዋል። ከተሰጡት አማራጮችም አንዱን ብቻ በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በሚታይ መልኩ ማጥቆር አስፈላጊ ነው።

***መመሪያ አንድ፡-*** ከዚህ በታች ለቀረቡ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጡ

፩.ስለ ጭውውት ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ብቻ ሃሳብ ይቀርብበታል።

ለ. የተለያዩ ሃሳቦችን በማንሳት ልምድን፣እውቀትን የምንለዋወጥበት ነው።

ሐ. መሪ ያስፈልገዋል።

መ. ሁለት ሰዎች ብቻ የሚያደርጉት ምልልስ ነው።

፪.የቋንቋ መሰረት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ድምፅ ለ. ፊደል ሐ. ትዕምርተ ምልክት መ. ሆሄ

፫.ለድምፅ መፈጠር አስተዋፅዖ የሌለው የቱ ነው?

ሀ. ከንፈር ለ. ጥርስ ሐ. ድድ መ. ደረት

፬. ሰውዬው አገም ጠቀም ነው። የተሰመረበት ቃል ዓውዳዊ ፍች -------- ነው።

ሀ. ልብስ ሰፊ ለ. ወላዋይ ሐ. ተንኮለኛ መ. ዝምተኛ

፭. በገላጭ ድርሰት ውስጥ ሊካተት የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. የህይወት ታሪክ ለ. የስፖርት ዜና

ሐ. የአንድ ነገር አሰራር ቅደም ተከል መ. የአንድ ሰው አካላዊ አቋም

፮. ሁለት ነገሮችን በመውሰድ አንድነታቸውን እና ልዩነታቸውን ለማሳየት የሚፃፍ የድርሰት አይነት የቱ ነው?

ሀ. ተራኪ ድርሰት ለ. ገላጭ ድርሰት ሐ. አመዛዛኝ ድርሰት መ. ስዕላዊ ድርሰት

፯. ከሚከተሉት ውስጥ አብዥ ምዕላድ የሆነው የቱ ነው?

ሀ.-ኣት ለ.-ኣዊ ሐ.-ኣማ መ.-ነት

፰. የቢ ጋር ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. እንደፈለግን ለመፃፍ ለ. ከርዕሱ እናዳንወጣ ይጠቅማል

ሐ. መቅረት የሌለበት ሃሳብ እንዳይቀር መ. ሃሳብን ከአላማ ለማገናኘት

፱. ከሚከተሉት ውስጥ አብዥ ምዕላድ የተጨመረበት ቃል የቱ ነው?

ሀ. አሸዋማ ለ. ልጅነት ሐ. ጠጠራማ መ. ካህናት

፲. ከሚከተሉት ውስጥ ስህተት የሆነው ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ካህናቶች ለ. ዲያቆናት ሐ. መምህራኖች መ. ዲያቆናቶች



LIVEWORKSHEETS

# ምንባብ

የሴት ድምፅ ሰማሁ፡፡በር ተከፈተ፡፡ኤልያስ ምንም ሳይናገር ገባ፡፡በር ተዘጋ፤ፈራሁ፡፡ትናት፣፣ ከትናት ወዲያ የማውቀው የማውቀው በጨለማ የተሞላው ሰንጣ የሚውጠኝ፣የቆምኩበት መሬት እንኳን ተንሸራቶ የሚሄድ፣የማላያቸው ብዙ እጅግ ብዙ አይኖች የታዘቡኝ መሰለኝ፡፡ እዚያ ከገባሁ በኋላ ነገም ከነገም ወዲያ ግንባሬ እና ጉንጬ ላይ የባለጌ ምልክት ጠባሳ ተፈጥሮ የሰራሁት ነገር ይገለጥብኝ ይሆናል እያልኩ ለራሴ፡፡ መሮጥ ተመኘሁ--ኤልያስ እንዲታሰበኝ ደሞ አልፈለኩም፡፡ኤልያስ የፈለጋት ሴት ሞታ ብትገኝ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ኤልያስ ሲወጣ “ያቺ ልኩህ ሴት ሞታ ስለተገኘች ያልኩህን ነገር ማድረግ አንችልም” ቢለኝ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ብዙ ሳይቆይ ተመልሶ ወጣ፡፡በሩ እንደተከፈተ ነበር፡፡በበሩ ቀዳዳ የማየው ደብዛዛ ብርሃን ጉድጓድ መሰለኝ፡፡ኩራዝ ግድግዳ ላይ ተሰቅሏል፡፡ሴትዮዋ ጥላ መስላ ትታየኛለች፡፡ኤልያስ ቀረበኝና “አትፍሪ እንኪይሔን”፡፡ዝቅ ብየ አየሁት፡፡በእጇ የሆነ ነገር ሊያሲዘኝ ይዳብሰኛል፡፡ብሮች ነበሩ፡፡ ለምን እንደሆነ ገብቶኝ መቀበል አፈርኩ፡፡የለመድኩት ጓደኛዬ እራሱ አሳፈረኝ፡፡ወደ ሴትዮዋ ለመግባት ተስማምቻለሁ፡፡ ወደ ጣር የምሄድ መሰለኝ፡፡ጥቁር ጣር፡፡ ሴትዮዋን አውቃት ነበር፡፡ ብዙ ጌዜ ከጉብታዬ ላይ ተቀምጬ የማያት፡፡ በጣም ቀይ ሴት ነበረች፡፡ከእሷ ይልቅ ቅላቷ የሚታይ፡፡ እውስጥ በከፊል ጨለማ ነበር፡፡የኩራዙ መብራት ባልተስተካከለ መልክ ይበራል፡፡ ደንገዝገዝ ያለ ቦታ መርጬ ሳላስበላ ቆምኩ፡፡ሴትዮዋ በሩን ዘግታ ወገቧን ይዛ እየሳቀች ታየኛለች፡፡ፀጉሯ ጀርባዋ ድረስ እንደጥቁር ወንዝ ይወርዳል፡፡ ፋርጣ የሆንኩ መሰለኝ፡፡ፋርጣ ሆንኩ እንጂ፡፡እጀን ዘርግቾ ብሮቹን ሰጠኂት እና ተቀመጥሁ፡፡ተቀብላኝ ለእኔ የማይታይ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠችው፡፡የቆሸሸ ወይም ቀለሙ ጥቁር የሆነ ጠረጴዛ ይሆናል፡፡የብሮቹ ድምፅ የበለጠ ስለ ስህተቱ የሚነግር አሉባልታ መሰለኝ፡፡መጋረጃ ገለጠችና አልጋ ዳር ቁጭ አለች፡፡ እድሜዋ ሰላሳ አይሆንም? ሳቋ ከፊቷ አልተነሳም፡፡ምን ያስቃል? እስቅነበር?

(አዳም ረታ፣ግራጫ ቃጭሎች፣ገጽ 156፣1997)

**መመሪያ ሁለት፡- ከላይ ቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቻቸውን በመምረጥ ፃፉ፡፡**

፲፩.ሳንጣ ሀ. አስፈሪ ለ. ሩቅ ሐ. ጨለማ መ. ሰፊ

፲፪.ሳላስበላ ሀ. ሳላስመዘግብ ለ. ሳላስነቃ ሐ. በድፍረት መ. ሳልሰጥ

፲፫.አፈርኩ ሀ. ተሸማቀኩ ለ. ፈራሁ ሐ. ደፈርኩ መ. አዘንኩ

፲፬.ደንገዝገዝ ሀ.ብርሃን ለ. ጨለም ያለ ሐ. አስፈሪ መ. በግልጽ የሚታይ

፲፭.ፋርጣ ሀ. አጣብቂኝ ለ. ጌጥ ሐ. አብረቅራቂ መ. አልማዝ

፲፮.ከጉብታዬ ሀ. ከፍ ያለ ቡታ ለ. የለመድኩት ሐ. ዝቅ ያለ መ. ሳራማ ቦታ

፲፯.እንዲታዘበኝ ሀ. እንዲገምተኝ ለ. እንዲያውቅብኝ ሐ. እንዲያሳፍረኝ መ. እንዲያየኝ

፲፰.አልተነሳም ሀ. አልተወገደም ለ. ፈገግ እንዳለች ሐ. ፀፅ ብላ መ. ሳተትዞር

፲፱.ጎድጓዳ ሀ. ዝቅ ያለ ለ. የሚያስፈራ ሐ. ሜዳማ መ. ሰፊ

፳.የባለጌ ምልክት ሀ. የሚያሳፍር ለ. ንቅሳት ሐ. ጠባሳ መ. የጠቆረ

፳፩.ከላይ የቀረበው አንቀጽ በየትኛው የድርሰት አይነት የቀረበ ነው?

ሀ. በተራኪ ለ. በገላጭ ሐ. በስዕላዊ መ. በአመዛዛኝ

፳፪.ምንባቡ በስንት አንቀጽ የተዋቀረ ነው?

ሀ. በአንድ ለ. በሁለት ሐ. በሶስት መ. በአምስት

**መመሪያ ሶስት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጡ።**

፳፫. ከሚከተሉት ውስጥ የዋህ አላፊ ጊዜን የሚያመለክተው ዓ/ነገር የቱ ነው?

ሀ. አንበሳ ገድሏል።　　ለ. አንበሳ ይገድላል።　　ሐ. አንበሳ እየገደለ ነው።

መ. ጠዋት አንበሳ ተገድሎ ነበረር

፳፬. የሰውየው ቤት በነገር ፈረሰ።የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ------ ነው።

ሀ. ተዛመመ　　ለ. ወደቀ　　ሐ. ተበጠበጠ　　መ. ተጋደመ

፳፭. ለቋንቋ መዋቅር መሰረቱ ምንድን ነው?

ሀ. ስርዓታዊነት　　ለ.ቃል　　ሐ.ድምጽ　　መ.ኃረግ

፳፮. ከላይ የቀረቡት ቃላት በፊደል ተራ ቅደም ተከተል በትክክል የተቀመጠው የቱ ነው?

ሀ. መ፣ሐ፣ለ፣ሀ　　ለ. ለ፣መ፣ሐ፣ሀ　　ሐ. ሐ፣ለ፣መ፣ሀ　　መ. መ፣ለ፣ሀ፣ሀ

፳፯.ከሚከተለሉት ውስጥ ድርብ ቃል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ቤተኛ　　ለ. መንገደኛ　　ሐ. ቤተሰብ　　መ. እግረኛ

፳፰.ድርብ ቃል ምንድን ነው?

ሀ. የሁለት ቃሎች ጥምር የሆነ　　ለ. ፍች የሌለው

ሐ. ትርጉሙ የማይታዎቅ　　መ. በመዝገበ ቃል ውስጥ የማይገኝ

፳፱. ከምንጽፈው እርስ ውጭ አላስፈላጊ ሃሳቦች እንዳይካቱ፣መቅረት የሌለበት ሃሳብ እንዳይቀር እና ሃሳብን እና አላማን ለማገናኘት የሚጠቅም ቅድመ ንድፍ ምንድን ነው?

ሀ. ርዕስ　　ለ. አንቀጽ　　ሐ. አስተዋጽዖ　　መ. ድርሰት

፴. ከሚከተሉት ውስጥ የትንቢት ጊዜን የሚያመለክተው ዓ/ነገር የቱ ነው?

ሀ. አንበሳ ገድሏል።　　ለ. አንበሳ እየገደለ ነው።

ሐ. አንበሳ ይገድላል።　　መ. አንበሳ ገድሎ ነበር።

፴፩.ሰውዬው ዘመድ አዝማድ ሌለው ነጠላ ነው።የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ------ ነው።

ሀ. ኩታ ሰሪ　　ለ. ብቸኛ　　ሐ. ጠላፊ　　መ. ወገኛ

፴፪.ይህ ልጅ ዝንጉ ነው። የተሰመረበት ቃል ዓውዳዊ ፍቺ ------- ነው።

ሀ. ፈጣን　　ለ. የሚረሳ　　ሐ. አስታዋሽ　　መ. ቀልጣፋ

፴፫.ከሚከተሉት ውስጥ ድርብ ቃል ሆነው የቱ?

ሀ. እድለኛ　　ለ. ነጭናጫ　　ሐ. ልብ-ወለድ　　መ. ልባም

፴፬. ሰውየው በልጁ ሆድ ጦሩን ወደወደው።የተሰመረበት ቃል ዓውዳዊ ፍቺ ---------- ነው።

ሀ. አስጠጋው　　ለ. ሆዱን ወጋው　　ሐ. አርቆ አስቀመጠጠው　　መ. አስቀመጠው

፴፭. ሰውየው ጠላት መስሏል። ሀ.የተሰመረበት ቃል ዓውዳዊ ፍቺ ------ ነው።

ሀ. ጠላሸት ነክቶታል　　ለ. ጠቁሯል　　ሐ. ገርጥቷል　　መ. ከስቷል

፴፮. ግጥም በአርኬ እንደሚከፋፈል ሁሉ ዝርው ጽሁፍ ደግሞ ------ ይከፋፈላል።

ሀ. በሃረግ　　ለ. በስንኝ　　ሐ. በአንቀጽ　　መ. በዓ/ነገር

፴፯.ክፉኛ ይህ ቃል በየትኛው የቃል ክፍል ውስጥ ይመደባል?

ሀ.ስም　　ለ. ግስ　　ሐ. ተውሳከ ግስ　　መ. መስተዋድድ

፴፰. ስነ ቃል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ተረት　　ለ. ግጥም　　ሐ. እንቆቅልሽ　　መ. አፈ ታሪክ



LIVEWORKSHEETS

፴፱. የአጭር ልቦለድ ባህሪ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሰፊ መቸት አለው ለ. ብዙ ገጸ ባህሪያት አሉት

ሐ. ሰፊ መቸት አለው መ. ነጠላ ውጤት

፵፩. ከሚከተሉት ውስጥ የአጭር ልቦለድ ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ነጠላ ውጤት ለ. ጥድፊያ ሐ. ቁጥብነት መ. ውስብስብ ሴራ

፵፪. የገጸ ባህሪያትን ነጠላ ህይዎት ሊያሳየን የሚችለው የአጭር ልቦለድ ባህሪ የሆነው የቱ ነው? ሀ. ሴራ ለ. ነጠላ ውጤት ሐ. ጥድፊያ መ. ቁጥብነት

፵፫. ምንዱባን በሚለው ቃል ውስጥ የተጨመረው አብኚ ምዕላድ የቱ ነው?

ሀ.-ኡ ለ.-ን ሐ.-ባን መ.-ኣን

፵፬. በስነቃል ውስጥ የሚካተተው የቱ ነው?

ሀ. ተውኔት ለ. ግጥም ሐ. አፈ ታሪክ መ. ልብ-ወለድ

፵፭. የሁነቶች ክስተት የሚፈጸምበት የልብ-ወለድ አላባ ምንድን ነው?

ሀ. ሴራ ለ. ግጭት ሐ. መቸት መ. ጭብጥ

፵፮. ምስል ከሳች ቃላትን ተጠቅመን የምንጽፈው የድርሰት አይነት ------- ነው፡፡

ሀ. ገላጭ ለ. ተራኪ ሐ. ስዕላዊ መ. አመዛዛኝ

፵፯. ከሚከተሉት ውስጥ ቅጽል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ወፍራም ለ. በላ ሐ. ቶሎ መ. በፍጥነት

፵፰. ከሚከተሉት ውስጥ ነፃ ምዕላድ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ቤት ለ. ቤቱ ሐ. ቤቴ መ. ቤቷ

፵፱. ከሚከተሉት ውስጥ ውስጠ ግንድ ቅጥያ የተጨመረበት ቃል የቱ ነው?

ሀ. አዋፍ ለ. መዘምራን ሐ. ነጫጭ መ. እፅዋት

፶. አንድ ደራሲ ለተደራሲያን የሚያስተላልፈው መልዕክት --------- በመባል ይታዎቃል፡፡

ሀ. ግጭት ለ. ሴራ ሐ. ጭብጥ መ. አንፃር

እየበዛ ሄደ ዘንድሮስ በራቸው፣

እንግዲህ ንጉሱ ምን ራስ አላቸው፡፡

፶፩. ከላይ የቀረበው ቅኔ ህብረ ቃሉ የቱ ነው?

ሀ. እየበዛ ለ. ምን ራስ ሐ. ንጉሱ መ. እየበዛ

፶፪. ከላይ የቀረበው ቅኔ ሰሙ -------- ነው፡፡

ሀ. አያስቡም ለ. የንጉሱ መሳፍንቶች ሞቱ ሐ. አዛዥ ጠፋ መ. ንጉሱ ሞቱ

እያሉ ካህናቱ ያርባ አራቱ ደብር፣

እንዴት ያለፍታት ተበረ ጎንደር፡፡

፶፫. ከላይ የቀረበው ቅኔ ህብረ ቃሉ ------- ነው፡፡

ሀ. ደብር ለ. ያለፍታት ሐ. ተቀበረ ጎንደር መ. ካህናቱ

፶፬. ከላይ የቀረበው ቅኔ ወርቁ ------- ነው፡፡

ሀ. እንዴት ሊሞት ቻለ

ለ. ጎንደርን ያህል አገር እንደት ድል ተመታ

ሐ. ሠው እንዴት ያለፍትሃት ይቀበራል

መ. ብዙ ካህን እያለ ፍትሃት አልተደረገገም



LIVEWORKSHEETS

፲፭.ከላይ የቀረበው ቅኔ ሰሙ ------- ነው፡፡

ሀ. ጎንደርን ያህል አገር እንደት ድል ተመታ

ለ. እንዴት ሊሞት ቻለ

ሐ. ብዙ ካህን እያለ ፍትሃት አልተደረገገም

መ. ሠውዬው ያለፍትሃት/ፍትሃት ሳይደረግለት ተቀበረ

፲፮. ቅኔን ከምንፈታባቸው ዘዴዎች ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. ታሪክን ጠንቅቆ በማወቅ

ለ. ቃላትን በመነጠል እና በማጣመር

ሐ. የመዝገበ ቃል ፍች በመጠቀም

መ. ለቃላት ሌላ ፍች በመስጠት

ይገድሉኝም እንደሁ ቆምኩኝ ከፊትዎ፣
ይሰቅሉኝም እንደው ቆምኩኝ ከፊትዎ፣
ያለም ጣም ምኒልክ ብዬ ሰደብኩዎ፡፡

፲፯. ከላይ የቀረበውን ቅኔ ምንን መሰረት በማድረግ ነው ልንፈታው የምንችለው?

ሀ. ቃሉን በማጥበቅ እና በማጥበቅ　　　ለ. ታሪክን በማወቅ

ሐ. በማጥበቅ እና በማላላት　　　መ. ለቃሉ ሌላ ፍች በመስጠት

፲፰. ከላይ የቀረበው ቅኔ ህብረ ቃሉ ------- ነው፡፡

ሀ. ምኒልክ　　ለ. ያለምጣም　　ሐ. ይሰቅሉኝም　　መ. ቆምኩኝ

፲፱. ከላይ የቀረበው ቅኔ ወርቁ ------- ነው፡፡

ሀ. አለምን የቀየረ　　ለ. ገዳይ　　ሐ. ጨካኝ　　መ. አዛኝ

፳. ከላይ የቀረበው ቅኔ ሰሙ ------- ነው፡፡

ሀ. ፊታቸው የተበላሸ　　ለ. የሚጣፍጥ　　ሐ. አስቀያሚ　　መ. አለምን የቀየረ



LIVEWORKSHEETS